በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ

ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ /የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

1. የመ/ቤቱ ተቀጣሪ ላልሆነ እና በሹፌርነት ለሚያገለግሉ ሠራተኛ በየወሩ ለኃለፊዎች ከመደበኛው ሰዓት ውጭ አገልግሎት ለሚሰጡ ሹፌር ልዩ አበል ብር 800.00 እንዲከፈል በመደረጉ የ5 ወራት በድምሩ ብር 4,000.00 አለአግባብ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል::
2. ለመስተንግዶ የአገልግሎት ግዥዎች የተከፈለ በድምሩ ብር 403,745.13 በወጪ የተያዘው አቅራቢዎች በማወዳዳር አሸናፊ ከሆነው ድርጅት ግዥ መፈፀም ሲገባው በቀጥታ እንዲገዛ መደረጉ ተረጋግጧል::
3. በግልፅ ጨረታ ግዥ መፈፀም ሲገባው፣ በውስን ጨረታ ለተፈፀሙ የተለያዩ የአገልግሎት ግዥዎች ብር 5,883,033.80 መከፈሉ ተረጋግጧል::
4. ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ግዥ መፈፀም ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት እንዲገዛ በመደረጉ ብር 58,479.60 በብልጫ ወጪ መደረጉን፣

5. በድምሩ ብር 1,536,778.73 ለተለያዩ አገልግሎቶች ግዥ በቅድሚያ የተከፈለው መ/ቤቱ አገልግሎቱን ከድርጅቶቹ ለማግኘቱ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ ተይዞ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡
6. ሚ/ር መ/ቤቱ ከተፈቀደለት በጀት ወጪ በማድረግ በራሳቸው በጀት ለሚተዳደሩ ተጠሪ ተቋማት በድምሩ ብር 1,094,595.66 ሥልጠና ለተሰጠበት እና የሕንፃ ግንባታ የአገልግሎት ክፍያ መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡
7. ለመ/ቤቱ 2 የወጭ አገር ኮንትራት ስራተኞች ከተከፈለው ደመወዝ ብር **267,814.00** ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የሥራ ግብር ብር 87,734.90 ሳይቀነስ እና ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡
8. በድምሩ ብር 2,027,158.85 በተገቢው የወጪ የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>ተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

9. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቀረበው የተሰብሳቢ ሂሳብ መግለጫ በሂሳብ መደብ 4210 ከተያዘው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 21,460,692.49 መወራረዱ ቢገለፅም ማስረጃው ባለመቅረቡ ለማረጋገጥ አለመቻሉን፣

<u>ተከፋይ ሂሳብ፣</u>

10. በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ቀናት እና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች ከተከፈለው ብር **3,029,718.64** ተቀናሽ መደረግ የሚገባው ከተከፋይ ሂሳብ የተቀነሰ ግብር በድምሩ ብር 4,839.43 ለሚመለከተው አካል ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፤ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- በበጀት ዓመቱ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣ ከመደበኛ በጀት ብር 43,141,087.23 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 29,920,168.53 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች፣

- ለቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች ቢን ካርድ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- በስቶክ ካርድ የሚታይ ከወጪ ቀሪ በቆጠራ ከሚገኘው ጋር በወቅቱ የማይመዛዘን መሆኑ፣
- በቋሚ ንብረት ክፍል የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች እንዲሁም የሚያገለግሉ እና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በአንድ ላይ ተቀላቅለው እንዲቀመጡ መደረጉ፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-00852 ተሽከርካሪ መኪና በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት ለ3 ወር እንዲቆም መደረጉን፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-1291 የሞተር ሳይክል ለረዥም ግዜ ያለአገልግሎት መቆየቱን፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4- 23002 መኪና ሊብሬው ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑን፣
- 4 ሠራተኞች የሚገለገሉባቸውን የተለያዩ ንብረቶች ሳያስረክቡ መ/ቤቱን የለቀቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

በ2008 ኦዲት ግኝቶች ላይ ስለተወሰደ የእርምት እርምጃ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥቅማ ጥቅም ለሚገባቸው የስራ ኃላፊዎች የቤት አበል፣ የኃላፊነት አበል እና አትዋላይዜሽን ክፍያ የፈጸመ ሲሆን፣ ከደመወዝ ጋር ተደምሮ የስራ ግብር መቀነስ ሲገባው ብር **90,260.03** ያልተቀነሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የመ/ቤቱን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የሪፓርቱ ዓላማ፣

የዚህ የሥራ አመራር ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የሚኒስትሩ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ለማድረግ ነው ፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት ኢንስቲትዩቱ ባዘጋጃቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ / የኦዲት አስተያየት / ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፣

- የሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ የሠፈሩት አሀዞችና ሪፖርቶችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመር፣
- የሥራ አመራሩ የሂሣብ ሪፖርቶቹን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸውን ጉልህ ግምቶች እና ውሣኔዎችን መመዘን፣

የሂሣብ አያያዝ ፖሊሲዎቹ ለሂሳብ ሪፓርቶቹ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሣብ ሪፖርቶቹ አግባብነት ያላቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የጸዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ የኦዲት አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሣብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የሚ/ር መ/ቤቱ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1.<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

1.1.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች፣</u>

የወጪ ሂሣቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ታህሳስ 2003 ዓ.ም ባወጣው የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች በወጪ የተያዘ በድምሩ ብር 2,027,158.85

በተገቢው የወጪ የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተራ ቁጥር	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ እና የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	ወጪው የተመዘገበበት የሂሣብ መደብ	መመዝገብ የነበረበት የሂሣብ መደብ	የገንዘቡ ልክ
1.	28/10/09	461019	የማስታወቂያ ክፍያ ለጥራት መሰራተ ልማት ፕሮጀክት (NQI)	6251	6253	823,172..50
2.	30/10/09	866026	የስፔስ ሰይንስ አጥር እና የቢሮ እድሳት ስራ	6251	6244	752,491.47
3	29/10/09	866013	የአጥርና የቢሮ እድሳት ክፍያ	6251	6244	451,494.88
4	30/03/09	-865611	የአየር ትኬት	**6417**	**6232**	437,197. 00
5	30/12/08	337726	**ለወሎአበል**	**6417**	**6231**	12,000. 00
				ድምር		**2,027,158.85**

1.1.2 <u>ስጋት፣</u>

- ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ ላያሳይ ይችላል፡፡
- የሂሳብ አያያዙ የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡:

1.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የማስታወቂያ ክፍያ በውል ቢፈፀምም በአርዕስቱ በጀት የተያዘለት በመሆኑ በ6253 መያዝ ይገባዋል፡፡ የስልጠና ወጪ በተያዘለት በጀት መያዝ ሲገባው፣ ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጉዳዮች ጋር ትስስር አለው በማለት በ6223 መያዙ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የአጥርና የቢሮ እድሳት ክፍያ ለጥገና በተያዘ በጀት በሂሳብ መደብ 6244 መያዝ ሲገባው፣ በውል የተፈፀመ አገልግሎት በመሆኑ በ6251 እንዲያዝ መደረጉ፣ ለሆቴል አገልግሎት እና ለአየር ትኬት መግዣ የተከፈለ ለሽልማትና ለሌሎች ክፍያዎች ከተያዘ

በጀት ወጪ ሆኖ በ6417 መያዙ የመንግሥት የፋይናንስ አያያዝ ሥርዐትን ያልተከተለ በመሆኑ የወጪዎች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ክፍያዎች ትክክለኛ የወጪ ሂሳብ አርዕስታቸውን የጠበቁ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

1.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

1) በጀቪ **461019** የወጪ መደብ 6251 (በውል የሚፈጸሙ የሙያ አገልግሎት) የተመዘገበበት ምክንያት በሀገራችን በጥራት ላይ ያለውን ግንዛቤ በህብረተሰቡ ላይ ለውጥ ለማምጣት እንዲያስችል በጥራት መሠረተ ልማት የሚገኙ አራቱ (4ቱ) ተጠሪ ተቋማት የፕሮሞሽን ስራ በአንድነት አቀናጅተው በጋራ እንዲያከናውኑ ለማድረግ ከዋፋ ማርኬቲንግና ፕሮሞሽን፤ ከ EBC እና ከፋና ፕሮሞሽን ጋር በተገባው ውል ስምምነት መሠረት የተከፈለ ክፍያ በመሆኑ እና ክፍያው በውል ላይ የተመሠረተ ስለሆነ፤ በውል የሚፈጸሙ የሙያ አገልግሎት ላይ እንዲከፈል ተደርጓል፡፡ ለመረጃ እንዲያገለግል ከዚህ መግለጫ ጋር የውል ሰምምነቱ በኮፒ **አባሪ (1)** ተያይዟል፡፡
2) በጀቪ **866026** የኢትዮጲያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት (የእንጦጦ ኦብዞቨ፟ራቴሪ) ክፍያ በተመለከተ ከ 6251 የሙያ አገልግሎት የተከፈለበት ዋና ምክንያት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር አማካኝነት በተገለፀው የወጪ ዝርዝር መመሪያ መደብ በሚገልፀው መሰረት ማለትም 6251 በመንግስት መ/ቤቶች የሚከናወን የካርታ እና የቅየሳ ስራ ሲከናወን ከዚህ ወጪ መደብ እንዲከፈል ይገልፃል፡፡ በዚህም መሰረት ለኢንስቲትዩቱ የቦታ ማካለል ስራ የተከናወነ በመሆኑ፤ከተጠቀሰው ወጪ መደብ 6251 እንዲከፈል ተደርጓል፡፡ ለመረጃ እንዲያገለግል ይህንን የሚግልፅ የወጪ ዝርዝር መመሪያ አንድ ገፅ **አባሪ (2)** ተያይዟል፡፡
3) በ JV **865598** ለተገለጸው የተፈጸመው ቀጥታ ግዥ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚገኙበት የ7^{ኛው} ዙር ሀገር አቀፍ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን የሽልማት ቀን በመሆኑና ለዝግጅቱ የሚያገለግል የተሻላሚዎች መፅሄት እና ፍኖተ ካርታ በዕለቱ ስለሚበተን እንዲሁም ካለው የጊዜ ሡሌዳ እንፃር እና አስቸኳይነት ተፈጻሚ ለማድረግ የተፈጸመ ቃጥታ ግዥ ነው፡፡ ለወደፊቱ የዚህ ዓይነት ግዥዎች ሲፈጸሙ በዕቅድና በውድድር ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡
4) በ **JV 174210** ከላይ በተ.ቁ (4) የተገለፀው ማሻሻያ ሃሳብ እደተጠበቀ ሆኖ በኦዲት ግኝቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተገለፀው ብር 494899.53 (ብር አራት መቶ ዘጠና አራት ሺ ህ

ስምንት ሞቶ ዘጠና ዘጠኝ ከ 53/100) ያልተከፈለ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ ለመረጃ እንዲያገለግል ጀቪ. 174210 ኮፒ **በአባሪ (4)** ተደርጓል፡፡

5) በ **JV 514677፤865611፤865632 እና 337726** የተፈፀሙት ክፍያዎች ከ 6417 የሆነበት ምክንያት በሀገር አቀፍ ደረጃ ክቡር ጠ/ሚ/ሩ የሚገኙበት በየዓመቱ አንድ ጊዜ የሚከናወን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሳምንት ስለሆነ፤ ይህ ዝግጅት እንዲካሄድ ከመንግስት የተመደበው በጀት በ 6417 ስለሆነ እና ይህ በጀት ሲፈቀድ በጥቅል በመሆኑ በተጨማሪም ከዝግጅቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ማንኛውም ክፍያዎች ከዚህ በጀት እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ለወደፊቱ በእያንዳንዱ የወጪ የበጀት ርዕስ እንዲፈቀድ በማድረግ ክፍያዎች እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

1.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

በተራ ቁ. 2 እና 3 የተያዘው ወጪ ለአጥር እና ለቢሮ እድሳት የተከፈለ በመሆኑ ከካርታ እና ቅየሳ ወጪ ጋር የማይዛመድ በመሆኑ ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡ በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች በመንግሥት የፋይናንስ አያያዝ ሥርዐት መሠረት እንዲመዘገቡ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.2.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>የመ/ቤቱ ባልደረባ ላልሆነ ሠራተኛ የተከፈለ አበል፣</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 8/ሀ የፋይናንስ ሥራን የሚያከናውነው ክፍል ኃላፊ እና የመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች የመንግስት ገንዘብ ለጸደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ እንደሚገባቸው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፣ የመ/ቤቱ ተቀጣሪ ላልሆኑ እና በሹፌርነት ለሚያገለግሉት ሠራተኛ በየወሩ ብር 800.00 እንዲከፈል በመደረጉ ከሀምሌ 1/2008 እስከ ህዳር 30/2009 የ5 ወራት በድምሩ ብር 4,000.00 አለአግባብ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

1.2.2 <u>ስጋት፣</u>

- ለመ/ቤቱ የተፈቀደው በጀት ለታቀደለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡
- የወጣው መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡

1.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ክፍያው በወጣው መመሪያ መሠረት መከፈሉን በመግለፅ ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም ሠራተኛው በመ/ቤቱ ለመቀጠራቸው እና የመ/ቤቱን ንብረት በኃላፊነት መረከባቸውን

የሚገልፅ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ለለአግባብ የተከፈለው አበል ተመላሽ እንዲደረግ እና የሠራተኛውን የቅጥር ሁኔታ በተመለከተ የሥራ አመራሩ ተገቢውን ማብራሪያ እንዲሰጥ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ሹፌሩ በተጠቀሱት ኃላፊ የሚፈለጉ ከሆነ በደንበ መሠረት ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በማዛወር ማሰራት የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡

1.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የቀድሞ ሚ/ር ሆነው ወደ መ/ቤታችን የመጡት ሚኒስትር ከሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል ወደ ሚኒስትር መ/ቤታችን ተሾመው በመጡበት ጊዜ ከደህንነት /Security/ አንጻር በአዋጅ ቁጥር 515/99 እና የሰቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በአወጣው መመሪያ መሰረት በተ.ቁ. 4.2 ላይ በተገለጸው በመንግስት ለተሾሙ ለበላይ ኃላፊዎች አገልግሎት የሚሰጡ በመደበኛ የስራ ቀናት አምሽተው የሚሰሩ እንዲሁም በዕረፍት ቀናትና በበዓል ቀናት ጭምር በመስራት በማንኛውም መንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰሩ ሹፌር ክፍያው የሚፈፀም እንደሆን ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሰረት ክፍያው ተፈፅሟል፡፡ ለመረጃ እንዲያገለግል የመመሪያውን ኮፒ እና ሹፌሩ መኪናውን የተረከቡበት እና ሲሄዱም ያስረከቡበት ማስረጃዎች አባሪ (5) በማለት ተያይዟል፡፡

1.2.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

የመ/ቤቱ ባልደረባ ላልሆነ ሰራተኛ የ5 ወር አበል ክፍያ መፈፀሙ አግባብ አለመሆኑንና ሠራተኛው የመ/ቤቱን ንብረት በሀላፊነት የተረከበበትን ማስረጃ እና የሰራተኛውን የቅጥር ሁኔታ በተመለከተ ማብራሪያ አልተሰጠም፡፡ አለአግባብ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.3.1 ግዥት፣ ያለውድድር በቀጥታ የተፈፀመ ግዥ፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1 የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት በፊደል /ሀ/ ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ታህሳስ 2008 ዓ.ም በተሻሻለው መመሪያ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 25.7 በፊደል ሀ የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ እቅድ ውስጥ ያልተካተቱ ዋጋቸው ከብር 5000 ያልበለጡ ዕቃዎችን

ወይም አገልግሎቶችን በቀጥታ ግዥ ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት መፈጸም እንደሚችሉ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመመሪያው መሠረት ግዥ የሚፈፅም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ ለተለያዩ የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥዎች የተከፈለ በድምሩ ብር 403,745.13 በተለያዩ ቀናት እና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች በወጪ የተያዘ ሲሆን አቅራቢዎች ተወዳድረው አሸናፊ ከሆነው ድርጅት ግዥ መፈፀም ሲገባው በቀጥታ እንዲገዛ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተቁ	ቀን	የደረሰኝ ቁጥር	ሂሳብ መደብ	የተሰጠ አገልግሎት	አገልግሎት ሰጪ ድርጅት	የገንዘብ መጠን
1	30/04/09	865598	6213	ህትመት	ጃጃው አታሚችና ዴቨሎፐርስ ኃ.የተ.የግ.ማ	141,245.50
2	25/09/09	865913	6233	መስተንግዶ	ለሒልተን ኢንተርናሽናል ሆቴል	152,419.97
3	20/08/09	514891	6233	መስተንግዶ	ለኦዳ ከፌ እናሬስቱሪንት	110,079.66
					ድምር	403,745.13

1.3.2 ስጋት፣

- ከደንብና መመሪያ ውጭ ግዥ በመፈፀሙ መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡
- አቅራቢዎችን በማወዳደር ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም መ/ቤቱ ሊያጣ ይችላል፡፡

1.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በበላይ አመራር ፈቃድ የሚፈፀሙት ግዥዎች በእቅድ ያልተያዙ እና የገንዘብ መጠናቸው በመመሪያው እንደተገለፀው መሆን ይገባዋል፡፡ ተመሳሳይ አገልግሎቶችን በአንድ በጀት ዓመት በተደጋጋሚ ከተወሰኑ አቅራቢዎች እንዲገዙ ማድረግ መመሪያን ያልተከተለ በመሆኑ ግዥ በእቅድ ተይዞ አቅራቢዎችን በማወዳደር እንዲፈፀም መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

- በ JV 514881 የተገለጸው ከዮሀንስ በዛብህ ተስፋዬ ማስታወቂያ የተሰራው በቀጥታ ግዥ የተከናወነ ሳይሆን በውድድር ላይ መሠረት ያደረገ የፕሮፎርማ ግዥ ሲሆን ለመረጃ እንዲያገለግል የፕሮፎርማውን ኮፒ እና ውሉን አባሪ (6) በማለት ተያይዟል፡፡
- በ JV ቁጥር 173920፣ 173908 ፣174210 እና 173919 ለፒራሚድ ሆቴል የተፈጸሙ ክፍያዎች ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የተፈጸሙ ሳይሆኑ ሚኒስትር መ/ቤቱ ለአንድ ዓመት ከሆቴሉ ጋር በገባው ውል መሠረት የተከናወነ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ክፍያ እና ግዥ ሲፈጸም በውድድር ላይ መሠረት ያደረገ መሆኑ እና በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ

እንዳልሆነ ከግንዛቤ ውስጥ እንዲገባልን እየጠየቅን፤ ለመረጃ እንዲያገለግል የውድድሩን ፕርፎርማ እና ውሉን አባሪ (7) ኮፒ ተያይዟል፡፡

- በ JV ቁጥር 865907 እና 172932 የተገለጹት ክፍያዎች ለራስ ሆቴል ሲፈጸሙ በቀጥታ ግዥ ሳይሆን ውድድርን መሠረት ያደረገ እና በውል ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባልን እየጠየቅን፤ለመረጃ እንዲያገለግል ፕርፎርማና ውሉን አባሪ (8) በኮፒ ተያይዟል፡፡
- የሂልተን እና ለአዳ ካፌና ሬስቶራንት ግዥዎችን በተመለከተ የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ አስተያየት ተቀብሎታል፡፡

1.3.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

- ከፒራሚድ ሆቴል ለተፈጸመው የአገልግሎት ግዥ በቀረበው ማስረጃ መሰረት ግዥው በግልጽ ጨረታ መከናወን ሲገባው በዋጋ ማቅረቢያ መከናወኑን አግባብ ሆኖ አልተገኘም ፡፡
- ከራሰ ሆቴል ለተፈጸመው የአገልግሎት ግዥ በቀረበው ማስረጃ መሰረት ግዥው በግልጽ ጨረታ መከናወን ሲገባው በዋጋ ማቅረቢያ መከናወኑን አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ከሁለቱ ሆቴሎች ለተፈፀመው የመስተንግዶ ግዥ ብር 2,352,377.0 ለፒራሚድ ሆቴል እንዲሁም ብር 763,596.19 ለራሰ ሆቴል ወጪ የሆነው ከግኝት ቁጥር 1.3.1 እንዲወጣ ተደርጎ በግኝት ቁጥር 1.4.1 ተይዟል፡፡

1.4.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በግልፅ ጨረታ መገዛት ሲገባው በውስን ጨረታ የተፈፀመ ግዥ፣</u>

ታህሳስ 2008 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የፌዴራል መንግሥት የዕቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 23.4 ግዥን በውስን ጨረታ ግዥ የሚፈፀመው የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለሁለት ጊዜያት ወጥቶ ምንም ተጫራች ያልቀረበ ወይም በድጋሚ ቢወጣ የቀረቡት ተጫራቾች በመ/ቤቱ የተዘጋጀውን የቴክኒክ ፍላጎት ያላሟሉ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ በመመሪያው መሠረት ግዥ የሚፈፅም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የእንጦጦ ኦብዘርቫቶሪና ምርምር ማዕከል አጥርና የቢሮዎች ጥገና ለማሰራት ተጫራቾችን በውስን ጨረታ በመጋበዝ ከአቶ መስፍን ግዛው ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ጋር በ24/09/09 ውል ገብቶ

ለተከናወነው የጥገና ሥራ በ30/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 866026 በሂሳብ መደብ 6251 በወጪ የተያዘ ብር **752,491.47** መከፈሉን፣

- በኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ከተማ የልዩ ተሰጥኦና ተውቦ ት/ቤት ግንባታ እና የሱፐርቪዥን ሥራን ለማሰራት ተጫራቾችን በውስን ጨረታ በመጋበዝ ከሌዊ ብርሀኑ አማካሪ አርክቴክቶችና ኢንጂነሮች ጋር በ08/07/09 ውል ገብቶ ለተሰጠው አገልግሎት በ30/09/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 516127 በሂሳብ መደብ 6251 በወጪ የተያዘ ብር 289,526.88 ክፍያ መፈጸሙን፣
- ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መ/ቤት ለግንባታ ዕድሳት እና በሮች ጥገና በውስን ጨረታ ካሸነፈው ከፖርታ ማኑፋክቸሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ውል ገብቶ ግዥ በመፈጸም በ30/08/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 865814 በሂሳብ መደብ 6223 ብር 1,273,547.38 ክፍያ መፈጸሙን፣
- ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ለስፔስ ሳይንስ የአጥርና የቢሮ እድሳትን ለማከናወን በውስን ጨረታ ካሸነፈው ከመስፍን ግዛው ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ጋር ውል ገብቶ በ29/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 866013 በሂሳብ መደብ 6251 የተያዘ ብር **451,494.88** ክፍያ መፈጸሙን፣
- በተለያዩ ቀናት እና በተለያዩ የክፍያ ማስመስከሪያዎች በወጪ የተያዘ እና ከፒራሚድ ሆቴል የመስተንግዶ ግዥ ለተፈፀመበት የተከፈለ ብር 2,352,377.0፣
- በቀን 25/09/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 865907 ብር 315,655.19 እንዲሁም በቀን 09/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 172932 ብር 447,941.53 በድምሩ ብር 763,596.19፣

በጠቅላላ ብር 5,883,033.80 በመመሪያው መሠረት በግልፅ ጨረታ ግዥ መፈፀም ሲገባው፣ በውስን ጨረታ ለተፈፀሙ የአገልግሎት ግዥዎች መከፈሉ ተረጋግጧል፡፡

1.4.2 ስጋት፣

- ከደንብና መመሪያ ውጭ ግዥ በመፈፀሙ መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡
- አቅራቢዎችን በማወዳደር ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም መ/ቤቱ ሊያጣ ይችላል፡፡
- በአቅራቢዎች መካከል ፍትሀዊ የንግድ ውድድር እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የመንግሥት መ/ቤቶች ግዥዎችን በግልፅ ጨረታ መፈፀም እንደሚገባቸው መመሪያው ቢያዝም የተወሰኑ አቅራቢዎችን በመጋበዝ በውስን ጨረታ እንዲገዙ

መደረጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም በወጣው መመሪያ መሠረት ግዥዎች እንዲፈፀሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.4.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

1.5.1 <u>ግኝት፣ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት የተፈፀመ ግዥ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ-28 ንዑስ አንቀጽ አንድ ለይ በማንኛውም የመንግስት ግዥ ለመሳተፍ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ከፊደል ሀ-ሰ የተዘረዘሩትን እና የመንግስት መ/ቤቶች ከግዥው ልዩ ባህርይ በመነሳት የሚያወጧቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት እንዳለበት ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም በአንቀጽ-16 ንዑስ አንቀጽ 16.21 ከፊደል ሀ-ረ ከተገለጹት ጥፋቶች ውስጥ አንዱን የፈጸመን ተጫራች የመንግስት መ/ቤቱ ከጨረታ ውጪ ማድረግ እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥ አፈፃፀም መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥን ለመፈፀም ከ3 ድርጅቶች የዋጋ ማቅረቢያ ተሰብስቦ አቅራቢዎች የተወዳደሩ ሲሆን፣

- ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ከካፒታል ሆቴል በብር 112,018.50 አገልግሎቱ እንዲገዛ መደረግ ሲገባው፣ በብር 170,498.10 ከሂልተን ሆቴል እንዲገዛ በመደረጉ ብር 58,479.60 በብልጫ ወጪ መደረጉን፣
- ሂልተን ሆቴል በሰጠው የዋጋ ማቅረቢያ እና አቅራቢዎች በተመረጡበት የዋጋ ማወዳደሪያ የተገለፀው የገንዘብ መጠን ብር 161,975.00 ሲሆን፣ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 173979 በወጪ የተያዘው ግን ብር 170,498.10 በመሆኑ ብር 8,523.10 ከተወዳደረበት ዋጋ በላይ በወጪ መያዙን ተረጋግጧል፡፡

1.5.2 <u>ስጋት፣</u>

- መመሪያን ያልተከተለ ግዥ በመፈፀሙ መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡
- በቀረበው ዋጋ መሠረት ግዥ አለመፈፀሙ በአቅራቢዎች መካከል ፍትሀዊ የዋጋ ውድድር እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.5.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

አገልግሎቱን ያቀረበው ድርጅት በውድድር አሸናፊ ከሆነው አቅራቢ የተሻለ እና ምቹ በመሆኑ እንዲሁም ሚ/ር መ/ቤቱ ተጨማሪ ስርቪስ በመጠየቁ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው አቅራቢ ግዥ መፈፀሙ በምላሹ ቢገለፅም አቅራቢዎች በሚወዳደሩበት ወቅት ተፈላጊ መስፈርቶች በግልፅ ተቀምጠው ማቅረብ መቻላቸው ሲረጋገጥ በዋጋ ማወዳደር ሲገባ አሸናፊው አቅራቢ ከተለየ በኂላ ተጨማሪ በሚደረጉ መስፈርቶች ውድድሩን ውድቅ በማድረግ አቅራቢውን ቀይሮ ግዥ መፈፀሙ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ሌሎች አቅራቢዎች የመሳተፍ ዕድል እንዳይኖራቸው በማድረግ ከመወዳደሪያ ዋጋ ውጭ ግዥ መፈፀም መመሪያን ያልተከተለ አሰራር በመሆኑ የወጣውን የመንግሥት መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ግዥዎች እንዲፈፀሙ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.5.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

1.6.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በወጪ የተያዘ የቅድሚያ ክፍያ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዝብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈጸሙ አስቀድሞ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የፅሑፍ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት እና በተገባው ውል መሠረት የሚከፈል ወጪ ከሆነ ሥራው መጠናቀቁ፣ የዕቃው ርክክብ መፈፀሙን ወይም አገልግሎት መሰጠቱ መረጋገጥ እንደሚገባው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ አያያዝ ሥርዐት መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- መ/ቤቱ ለአጥር ግንባታ እና ለጥገና ሥራዎች ከመስፍን ግዛው ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ጋር በገባው ውል መሰረት የውሉ ጠቅላላ ዋጋ ብር 1,504,982.94 30% ብር 451,494.88 ለተቋራጩ በቅድሚያ የተከፈለ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በቀን 29/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 866013 በሂሳብ መደብ 6251 በወጪ ተይዞ መገኘቱን፣
- ለቢሮ እድሳትና ጥገና ከፖርታ ማንፋክቸሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ጋር መ/ቤቱ በገባው ውል መሠረት የውሉን ዋጋ ብር 2,547,094.75 50% በቅድሚያ የተከፈለ ብር

1,085,283.85 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በቀን 30/08/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 865814 በሂሳብ መደብ 6233 በወጪ ተይዞ መገኘቱን፣

በድምሩ ብር 1,536,778.73 ለተለያዩ የአገልግሎቶች ግዥ በቅድሚያ የተከፈለ ሲሆን መ/ቤቱ አገልግሎቱን ከድርጅቶቹ ለማግኘቱ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተይዞ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

1.6.2 ስጋት፣

የሒሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የበጀት ዓመቱን የወጪ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

1.6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለግንባታ እና ለጥገና ሥራዎች ለተጠቀሱት ተቋራጮች የተሰጠ የቅድሚያ ክፍያ ግንባታው ወይም የጥገና ሥራው ሲጠናቀቅ ለተሰራ ሥራ ከሚከፈለው ክፍያ ተቀናሽ መደረግ የሚገባው በመሆኑ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው፣ የተሰብሳቢ ክምችት እንዳይፈጥር በሚል በወጪ እንዲያዝ በመደረጉ የፋይናንስ አያያዝ ሥርዐትን ያልተከተለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በተሰብሳቢ ተይዞ ተገቢው ማስረጃ ሲቀርብ በወጪ እንዲመዘገብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

1.7.1 ግኝት፣ በበጀት ለሚተዳደሩ መ/ቤቶች ተከፍሎ የተገኘ፣

በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የመ/ቤቱ የሂሳብ አያያዝ ሥርዐት መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ለኢትዮጲያ ደራጀዎች ኤጀንሲ ሠራተኞች ስልጠና ለተሰጠበት ለዲኪውኤስ ማኔጅመንት ሰርቪስ ኃ/የተ/የግ/ማ የተከፈለ ብር 542,595.66 በ25/09/2009 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 460922 በሂሳብ መደብ 6271 በወጪ የተያዘ መሆኑን፣

- በ29/10/200 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 461029 በሂሳብ መደብ 6251 በወጪ የተያዘ ብር 552,000.00 ለኢትዮጲያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የህንፃ ግንባታ የተከፈለ መሆኑን፣

በድምሩ ብር 1,094,595.66 ሚ/ር መ/ቤቱ ከተፈቀደለት በጀት ወጪ በማድረግ በራሳቸው በጀት ለሚተዳደሩ ተጠሪ ተቋማት የአገልግሎት ክፍያ መፈፀሙን ተረጋግጧል፡፡

1.7.2 ስጋት፣

- ለመ/ቤቱ የተፈቀደለት በጀት ለታቀደለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡
- የወጣው የበጀት አጠቃቀም መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡

1.7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

መ/ቤቱ በጀት ለተፈቀደላቸው ድርጅቶች የአገልግሎት ግዥ መፈፀሙ የበጀት አያያዝ ሥርዐቱን ያልተከተለ አሰራር ተግባራዊ መደረጉን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ክፍያውን በተመለከተ የሥራ አመራሩ ተገቢውን ማብራሪያ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

1.7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

በሚ/ር መ/ቤታችን በኩል የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በጥራትና መሠረተ ልማት (NQI) ፕሮግራም በጀት ሲፈቀድልን በሚ/ር መ/ቤቱ ስር ለሚገኙ ተጠሪ ተቋማት ማለትም የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ፤ የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና፤ የብሄራዊ ስነ-ልክ ኢንስቲትዩት እና የአክርዲቴሽን ፅ/ቤት የጋራ መግባቢያ ሰነድ /ውል/ በመፈራራም ጥራትን በሀገራችን እንዲያድግ በማድረግ ወጪና ገቢያችን **/Import and Export Substitution /** ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም በዚሁ የጋራ ስምምነት መነሻ በማድረግ በ BPV ቁጥር 460922 እና 461029 የተጠቀሱት ክፍያዎች በውል /በስምምነቱ / መሠረት የተፈጸሙ ክፍያዎች ናቸው፡፡ ለዚህም ለሁለቱ መ/ቤቶች የባለሙያ እና የአቅም ግንባታ ስራዎች የተከናወኑ መሆናቸውን ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባልን እየጠየቅን ለወደፊቱም (NQI) በጀት በመንግስት ሲመደብ ለዋናው መ/ቤት ብቻ እንዳልሆነ ግንዛቤ ውስጥ እንዲገባልን እንጠይቃለን፡፡

1.7.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ሚ/ር መ/ቤቱ በስሩ ላሉ አራት መስሪያ ቤቶች ለጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት የሥራ ማስኬጃ በጀት በሚ/ር መ/ቤቱ ሥም እንደሚያስፈቅድ እና በውል /በስምምነቱ / መሠረት ለሚፈጸሙ ክፍያዎች ወጪ እንደሚያደርግ ከሥራ አመራሩ በተሰጠው ምላሽ እና በኦዲቱ

የመውጫ ውይይት ወቅት የተገለፀ ቢሆንም ሚ/ር መ/ቤቱ ለተጠቀሱት መስሪያ ቤቶች ክፍያ እንዲፈፅም የገባው የውል ስምምነት ሊቀርብ አለመቻሉ ታውቋል፡፡

1.8.1 ግኝት፣ ተቀናሽ ያልተደረገ የሥራ ግብር፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባወጣው በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 የመንግስት መ/ቤቶችና ልማት ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች ድርጅቶችና ተቋማት ከተቀጣሪዎቻቸው ሊቀንሱት የሚገባውን የሥራ ግብር በተመለከተ ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ ለመ/ቤቱ 2 የወጭ አገር ኮንትራት ስራተኞች በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 865855 እና 865891 ከተከፈለው ብር **267,814.00** ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የሥራ ግብር ብር 87,734.90 ለሚመለከተው አካል ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

1.8.2 ስጋት፣

- ተቀናሽ መደረግ የሚገባው ግብር ለሚመለከተው አካል ገቢ ባለመደረጉ የመንግስት የገቢ አሰባበሰብ ሥርዐት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡
- የወጣው የገቢ አሰባሰብ ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡

1.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የሥራ ግብር ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ ተደርጎ ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ገቢ መደረግ ይገባዋል፡፡ ለወደፊቱም በደንቡ መሠረት ተቀናሽ እንዲደረግ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.8.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሣብ፣

2.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት ሂስብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ ቁጥር 4 ተሰብሳቢ ሂሳብ (መ) ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሰብ መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንደሚገባው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ በሚ/ር መቤቱ

በሂሳብ መደብ 4210 በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሌሎች የቅድመ ክፍያዎች የሂሳብ አርዕስት በተሰብሳቢ የተያዘ እና በውል ስምምነት መሠረት ለምርምር ሥራዎች የተከፈለ ብር 58,244.085.94 ከ4 ወራት በላይ ሳይወራረድ መቆየቱ ታውቋል፡፡

2.2 <u>ስጋት፣</u>

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በተሰጠው የኦደት አስተያየት መሠረት በተሰብሳቢ ከተያዘው ሂሳብ ብር 15,098,494.92 ማስረጃው ቀርቦለት የተወራረደ መሆኑ በተሰጠው ምላሽ ቢገለፅም ማስረጃው ለኦዲቱ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ለተወራረደው ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ እና ቀሪው በተሰብሳቢ የሚታያው እንዲወራረድ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

በ 2008 እና በ2009 ዓ.ም በጀት ለሀገራዊ ችግር ፈች የምርምር ፕሮጀክቶች ለረጅምና ጊዜያት በውል የሚፈጸም የምርምር ድጋፍ ሲሆን የተደገፉት ድጋፍ የፋይናንስና ፊዚካል አፈፃፀማቸው እየተገመገመ የፋየናንስ አፈጻጸመቸውን የሚያቀርቡ በመሆኑ እስከ አሁን በተሰብሳቢ ከተያዘው ብር 58,244,085.94 (ሃምሳ ስምንት ሚሊያን ሁለት መቶ አርባ አራት ሺህ ሰማኒያ አምስት ከ94/100) ውስጥ ብር 21,460,692.49 (ሃያ አንድ ሚሊየን አራት መቶ ስልሳ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከ49/100) በውስጥ ኦዲት አስተያየት መሠረት (Statement of Expenditure) ቀርቦለት ማወራራጃ የተሰራለት ሲሆን ቀሪ ያልተወራራዱ ሂሰቦችም ክትትል እየተደረገበት ይገኛል፡፡መረጃው ብዙ ከመሆኑ አንዓር አባሪ (12) ተያይዟል፡፡

2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቀረበው የተሰብሳቢ ሂሳብ መግለጫ በሂሳብ መደብ 4210 ከተያዘው ብር 58,244,085.94 በውስጥ ኦዲት አስተያየት መሠረት (Statement of Expenditure) ቀርቦለት ብር 21,460,692.49 የተወራረደ መሆኑ በተሰጠው ምላሽ የተገለፀ ቢሆንም ከምላሹ ጋር በአባሪ የቀረበው ማስረጃ ሂሳቡ በወጪ የተያዘበት የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ብቻ በመሆኑና ገንዘቡ ለታቀደለት የምርምር ሥራ ለመዋሉ የቀረበ ዝርዝር መረጃ እና ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

3. ተከፋይ ሂሳብ፣

3.1 ግኝት፣ ተቀናሽ ያልተደረገና ለሚመለከተው አካል ያልተከፈለ ታክስ፣

የፌዴራል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 አንቀጽ 53 ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት ንዑስ አንቀጽ 1.በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፣ የመንግስት መ/ቤቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚኒስትሮች ም/ቤት በሚያወጣው ደንብ ግብር ተቀንሶ ቀሪ እንዲደረግበት ከተወሰነ ማናቸውም ክፍያ ግብሩን ቀንሰው ማስቀረት እንደሚገባቸው ይገልፃል። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3. ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት አካል በወሩ ውስጥ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ቀሪ መደረግ የሚገባውን ሂሳብ ከወሩ መጨረሻ ጀምሮ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለበት ያዛል። ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚፈፅማቸው የእቃ እና የአገልግሎት ግዥዎች ግብርን ተቀናሽ የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ቀናት እና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች ከተከፈለው ብር **3,029,718.64** ተቀናሽ መደረግ የሚገባው ከተከፈይ ሂሳብ የተቀነሰ ግብር በድምሩ ብር 4,839.43 ለሚመለከተው አካል ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል። በ2008 በጀት ዓመት ኦዲትም ተቀናሽ መደረግ የሚገባው ግብር ሳይቀነስ መቅረቱን በመግለፅ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ ለተሰጠው የኦዲት አስተያየት የሥራ አመራሩ በሰጠው ምላሽ ስህተቱ እንደማይደገም እና አሰራሩ እንደሚስተካከል ቢገለፅም እርምጃ ባለመወሰዱ በ2009 በጀት ዓመትም ተቀናሽ ሳይደረግ መገኘቱ ታውቋል። ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል።

	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ (የሂሳብ ምዝገባ ማዘጋጃ) ቁ	የገንዘብ መጠን	የወጪ ምክንያት	ከተከፈይ ሂሳብ የተቀነሰ	ከተከፈይ ሂሳብ መቀነስ የሚገባው	ያልተቀነሰ ልዩነት
1	1/02/09	173908	294,252.25	ለፒራሚድ ሆቴል	4,652.20	5,117.43	465.23
2	21/06/09	174210	487,977.17	ለፒራሚድ ሆቴል	7,715.03	8,486.56	771.53
3	4/02/09	173920	1,084,549.50	ለፒራሚድ ሆቴል የመስተንግዶ	17,147	18,861.73	1,714.73
4	30/10/09	866159	179,996.88	ኤም.ት.ድ.ኤን ድርም ለይኔር ሆቴል	2,845	3,130.38	285.38
5	30/02/09	173919	485,598.08	ለፒራሚድ ሆቴል	7,676.81	8,445.18	768.37
6	30/05/09	174195	146,652.83	ለራስ ሆቴል	2,318.62	2,550.48	231.86
7	1/02/09	173914	342,409.97	ለፒራሚድ ሆቴል	5,413.39	5,954.96	541.57
8.		73940	8,281.96	ለሞኢንኮ	83.27	144.03	60.76
	ድምር		**3,029,718.64**				4,839.43

3.2 <u>ስጋት፣</u>

- መንግሥት ሊያገኝ የሚገባው ገቢ በወቅቱ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡
- የወጣው መመሪያና አዋጅ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡

3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

የሠራተኞች የአገልግሎት ክፍያዎች በመሆናቸው ታክስ መቀነስ እንደማይገባው አቅራቢዎች በመግለፃቸው ከመንግሥት ገቢ ተቀናሽ ተደርጎ ለአቅራቢው እንዲከፈል መደረጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተቀናሽ መደረግ የሚገባዉ ሂሣብ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ተመላሽ ተደርጎ ለገቢ ሰብሳቢው ባለሥልጣን ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

4.<u>በጀት፣</u>

4.1 <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በበጀት ዓመቱ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣ በየሂሳብ መደቦቹ ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 43,141,087.23 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 29,920,168.53 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

4.2 <u>ስጋት፣</u>

- በበጀት ዓመቱ ተራፊ በጀት መገኘት በሌሎች መ/ቤቶች ሊሠራበት የሚችለውን በጀት በመ/ቤቱ ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡
- የተፈቀደው በጀቱ በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ አለመደረጉ የመ/ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በሂሳብ መደብ 6253 መያዝ የሚገባው ወጪ በ6251፣ በ6244 መያዝ የሚገባው በ6251 በመያዙ እንዲሁም በሂሳብ መደብ 6252 ለቴክኖሎጂ ሽግግር ከተመደበው ካፒታል በጀት ለአዳራሽ ኪራይ ወው መደረግ ሲገባው ከ6417 በመከፈሉ በእነዚህ እና በሌሎችም የሂሳብ አርዕስቶች የወጪ ሂሳቦች በተገቢው የሂሳብ መደብ ባለመመዝገባቸው በሥራ ላይ ሊውል የሚችል በጀት ሳይሰራበት ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

5.ንብረት፣

5.1.1 ግኝት፣ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ፣

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የንብረት አስተዳደር እና አጠባበቅ በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ለቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች ቢን ካርድ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- በስቶክ ካርድ የሚታይ ከወጪ ቀሪ በቆጠራ ከሚገኘው ጋር በወቅቱ የማይመዛዘን መሆኑ፣
- በቋሚ ንብረት ክፍል የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች እንዲሁም የሚያገለግሉ እና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በአንድ ላይ ተቀላቅለው እንዲቀመጡ በመደረጉ ለሥራ አመቺ አለመሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የተሽከርካሪዎችን አያያዝ በተመለከተ፣

- የሰሌዳ ቁጥር 4-00852 ተሽከርካሪ መኪና በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት ለ3 ወር እንዲቆም መደረጉን፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-1291 የሞተር ሳይክል ለረዥም ግዜ ያለአገልግሎት መቆየቱን፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4- 23002 መኪና ሊብሬው ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑን፣

ለማጋገጥ ተችሏል፡፡

መ/ቤቱን ከለቀቁ ሠራተኞች ተመላሽ መደረግ የሚገባቸውን ንብረቶች በተመለከተ፣

መ/ቤቱን የሚለቁ ሠራተኞች በእጃቸው የሚገኙ ንብረቶችን በአግባቡ ለመ/ቤቱ መመለሳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ 4 ሠራተኞች የሚገለገሉባቸውን የተለያዩ ንብረቶች ሳያስረክቡ መ/ቤቱን የለቀቁ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የለቀቁ ሰራተኞች ስም	ያልተመለሱ ንብረቶች ዝርዝር	ብዛት	የንብረቱ ተከታታይ ቁጥር
1	ርብቃ ዳንኤል	ላብቶፕ ሊኖቫ	01	Most-101-4531-01psm-
		ፍላሽ 4ጊቢ	01	
		የቆዳ ቦርሳ	01	
		ብራዘር ፕሪንተር	01	Most-101-4531-02-psm-127
		ዴል ኮምፒተር	01	Most-101-4531-01-psm-318
		የኮምፒትር ተረፔዛ	01	Most-101-4531-02-psm-127
		ተረፔዛ ከነሞባይል ሼልፊ	01	Most-101-4531-11-psm-208
2	ደረጀ ሽማረ	ዴል ኮንፒተር	01	Most-101-4531-01-psm-70
		ኮፊ ቴብል	01	Most-101-4531-13-ps-48
		ጠረጴዛ የኤክሰፐርት	01	Most-101-4531-11-psm-157
		ፕሪንተር fs 11200	01	Most-101-4531-02-ps-75
		ፍላሽ 4ጊቢ	01	
3	እንዳለ መኮንን	ላፕቶፕ ኮምፒውተር		Most-101-4531-01-pRS-195
		ቶሽባ ላፕቶፕ		Most-101-4531-01-HR-34
		ፍላሽ 4ጊቢ	01	
		ተንጠልጣይ ቦርሳ		
		ማናጀሪያል ተረቤዛ		Most-101-4531-11-HR-102
		ተሽከርካሪ ወንበር		Most-101-4531-12-HR-215
4	ጌታሁን ተፈሪ	HP ላፕቶፕ ኮምፒውተር	01	Most-101-4531-01-TTD-311
		ጠረጴዛ የኤክሰፐርት	01	Most-101-4531-11-TTD-160
		ፍላሽ 8ጊቢ	01	
		UPS 700V	01	Most-101-4531-04-TDT-210
		ዴል ኮንፒተር	01	Most-101-4531-01-TTD-107

5.1.2 ስጋት፣

- በንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሠረት ንብረቶች በአግባቡ ባለመጠበቃቸው ለብክነት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡
- በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለግለሰቦች ጥቅም በመዋላቸው የመንግሥት ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡

5.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች ቢን ካርድ ተዘጋጅቶ ተገቢው ምዝገባ እንዲከናወን እና ከወጪ ቀሪው ከዕቃዎች ቆጠራ ጋር እንዲመሳከር መደረግ ይኖርበታል፡፡ የሚያገለግሉ እና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች እንዲሁም ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች ተለይተው እንዲ ቀመጡ ሊደረግ ይገባል፡፡ በብልሽት የቆሙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው ለአገልግሎት እንዲበቁ እና ሊብሬ ያልቀረበላቸው 2 ተሽከርካሪዎች ከሚመለከተው አካል ተጠይቆ እንዲቀርብ ክትትል መደረግ ይገባዋል፡፡ መ/ቤቱን ከለቀቁ ሠራተኞች መካከል የተረከቧቸውን ንብረቶች ተመላሽ ያደረጉ ለመሆኑ ማስረጃ ቢቀርብም የተመለሱት 2 ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች ሲሆኑ በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰው የኮምፒዩተር መለያ ቁጥር የሌለው እና በተራ ቁጥር 2 የተገለፀው በመጠቀሚያ ካርድ ከተመዘገበው የተለየ መለያ ቁጥር ያለው ሆኖ በመገኘቱ ከመ/ቤቱ የተረከቧቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ሁኔታው ተጣርቶ ገቢ የተደረጉት ንብረቶች ትክክለኛነት እንዲረጋገጥ እና ተመላሽ ያልተደረጉት እንዲመለሱ ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

5.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

6 ልዩ ልዩ፣

6.1.1 ግኝት፣ በቅጥርና በደረጃ ዕድገት ያልተሟሉ ክፍት የሥራ መደቦችን በተመለከተ፣

የመንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች ቁጥር 8/2008 የመንግስት መስሪያ ቤት የሰው ኃይሉን በቅጥር ለማሟላት፣ ለማስተዋወቅ፣ ለማሰልጠን፣ ለመቆጣጠር፣ ለመገምገም፣ ለማማከር፣ ለማሳደግ፣ ለመካስ፣ በዲሲፕሊን ለመቅጣት፣ለማሰናበት እና ለመሳሰሉት አስተዳደራዊ ሥራዎች ተስማሚ ፖሊሲዎችንና የአፈጻጸም መመሪያዎች ሊኖሩት እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዕቅድ የያዛቸውን ተግባራት በአግባቡ ለመፈጸም ይችል ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በሰው ኃይል መሙላት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ከተፈቀደለት 353 የስራ መደቦች ውስጥ የሰው ኃይል የተመደበው በ195 መደቦች በመሆኑ 158 የሥራ መደቦች (44.76%) ክፍት መሆናቸው ታውቋል፡፡

6.1.2 <u>ስጋት፣</u>

መ/ቤቱ በበቂ የሰው ኃይል ባለመደራጀቱ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሚጠበቅበትን ተግባር በአግባቡ እንዳይወጣ ያደርገዋል፡፡ የተቋቋመለትን ዓላማ ላያሳካ ይችላል፡፡

6.1.3 <u>**የማሻሻያሀሳብ፣**</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲሞሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6.1.4 <u>**የሥራ አመራሩ ምላሽ፣**</u>

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

6.2.1 <u>**በ2008 ኦዲት ግኝቶች ላይ ስለተወሰደ የእርምት እርምጃ፣**</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2016 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰረት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡በዚሁ መሰረት በመ/ቤቱ የ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ ስለመወሰዱ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥቅማ ጥቅም ለሚገባቸው የስራ ኃላፊዎች የቤት አበል፣ የኃላፊነት አበል እና አኑዋላይዜሽን ክፍያ የፈጸመ ሲሆን፣ ከደመወዝ ጋር ተደምሮ የስራ ግብር መቀነስ ሲገባው ብር 90,260.03 ያልተቀነሰ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

6.2.2 <u>ስጋት፣</u>

- መ/ቤቱ ለኦዲት ሪፖርት የሚሰጠውን ትኩረት ሊያሳንሰው ይችላል፡፡
- በሪፖርት በሚሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶች መሰረት እርምጃ ያለመውሰድ ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል፡፡

6.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳይሰበስብ የቀረውን ግብር በመሰብሰብ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ ማድረግ ይገባል፡፡

6.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!!